# ስሙ ይባረክ !

ከንግሥት ገ/ሕይዎት

9/14/2008

ይድረስ ለኢ/ር ኃይሉ ሻውል እና
ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አመራር አባላት
እንዲሁም ደጋፊዎችና ቤተሰቦች በሙሉ

አዲሱ የፓርቲያችን ስም ከስሞች ሁሉ በላይ ነው፡፡

ይህንን ስል "መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት" የሚለው ስም ቀደም ሲል የነበረ በመሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ ስሙ ገላጭና ጥርት አድርጎ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወክል በመሆኑ እንጅ፡፡

ምን ነካሽ ባትሉኝ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀብሎትና አምኖበት ብሎም ተሰባስቦበት የነበረው "የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ" የሚለው ስም በውስጡ አንድ ነገር እንደሚጎድለው ይሰማኝ ነበር፡፡ በነበረው የጊዜ መጣበብ እና ውክቢያ ምክንያት አንኳንስ እንደዚህ ዓይነቱን ጥያቄ አንስቶ ለማስተካከል ቀርቶ አንኳር ጉዳዮች ላይ እንኳ ማስተዋል ተስኖን በድካማችን የከፈልነውን ያህል ሳናተርፍ ቀርተናል፡፡ ምንም እንኳ በስም ማውጣቱ ላይ ተገኝቼ ሃሳቤን ለመስጠት ባልችልም ይህ ጉዳይ በውስጤ ሲብላላና ሲመላለስ እንዳለ በውስጣችን የነበረው ቆሻሻ እየነተፈ ሲመጣና በፓርቲው ውስጥ የነበረው አሰላለፍ ሲለይለት ያን ጊዜ "ኢትዮጵያ" የሚው ቃል ለምን በፓርቲው ስም ውስጥ እንዳልተጠቃለለ እየገባኝ መጣ፡፡

ኢትዮጵያ የሚለውን ስምና ታሪክ ለማጥፋት ወይም እንዳልነበር ለማድረግ ታጥቀው የተነሱትና እንዴውም ኢትዮጵያ የሚባል የአገር ስም የለም የመድፍ ስም እንጂ የሚሉት አምባገነን መሪዎቻችን ለምን ስሙን አንደሚጠሉት ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጥንት ለትግል ብለው ሲነሱም የመጀመሪያ ዓላማቸው አገራችንን በኀሳ ከፋፍለው ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር ለማድርግ በመሆኑ ከዚህም አልፎ ለተግባር ማከናወኛ ይሆናቸው ዘንድ አንቀጽ 39ን በሕግ ማስቀመጣቸው ዓይነተኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ ሆኖም ግን መድረሻ ያጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅንጅት ይዞት የወጣው መተዳደሪያ ደንብና ማኒፌስቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ በደልና ጉዳት የዳሰሰ ስለነበር በድርጅቱ ዙሪያ በመሰባሰብና እምነቱን በመጣል በምርጫ 97 በዚህ ስም የሠራውን

EthioLion.Com

EthioLion

ታምር እኛ ብቻ ሳንሆን የዓለም ማህበረሰብ ያውቃል:: ግን ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በድርጅታችን ስም ውስጥ ሳይጠቃለል ለምን ቀረ?

በተቀነባበረ ሴራ በአመራሮች በአባላትና እንዲሁም በድርጅቱ ላይ የደረሰውን አደጋና የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለው መስዋዕትነት ታሪካዊ ቢሆንም በተለያዩ ሚዲያዎች የተነገሩና ሕዝቡም የተወያየባቸው ጉዳዮች በመሆናቸው አንደገና በማንሳት ወደኋላ ለመውሰድ አልፈልግም :: ታዲያ ለምን ይሆን አሁንም አዲስ የተፈለፈሉ ፓርቲዎች ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል በስማቸው ውስጥ ያላስገቡት? ምክንያቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመርምረው::

ከላይ በጠቀስኩት ምክንያት በዚህ ስም ውስጥ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በመገኘቱና ቀደም ሲል የነበረኝን ቅሬታ ያስወገደ በርግጥም ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ለማንም ሰው የሚያስረዳ ስለሆነ በስሙ እረክቻለሁ::

ስምን መላክ ያወጣዋል እንዲሉ አንባገነን መሪዎቻችን ቃሉን ቢቀሙንም ዓላማና ግባችን መንጠቅ ስለማይችሉ ወደ ተሻለ ስም በመሸጋገራችን ደስ ሊለን ይገባል:: ለኔ ኢትዮጵያ በሚለው ስም ውስጥ ብዙ መልዕክቶችና ሚስጥሮች አሉበት::

ለምሳሌ :- ጣሊያንን የሚያክል ታላቅ አገር ድል የነሳ ስም

- ከረጂም ዘመን አንስቶ በአበበ ቢቂላና በሌሎች ጀግኖች አትሌቶች ድል ባነዲራ የተውለበለበለት ስም
- በአፍሪካ አንድነት ምስረታ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘ ስም
- ከ80 በላይ ብሔረሰብና ቋንቋ የሚገኝበት ስም
- የራሷ ፊደልና የቀን መቁጠሪያ ያላት አገር ስም :: እረ ስንቱ ይህን ስም ይኮሩበታል እንጂ ይጸየፉታል ወይ? ስለዚህ ስሙ በእርግጥም ስም ነው:: ገላጭነው::

ታዲያ ወገኖቼ መከፋፈልና መለያየትን የተጠቀሙበት የዓለም ክፍሎች አክሳሪ መሆኑን በመገንዘብ ትላልቅ አገሮች ሳይቀሩ በአህጉር ደረጃ በሚሰባሰቡበትና የሰውነት (ኢንተርናሽናሊዝም) ፍልስፍና እየጎላ መጥቶ ዓለም አንድ መንደር እንደምትሆን በሚሰበክበት ወቅት እንደልኳንዳ ሥጋ በትዕዛዝ እየተመደብን ለድህነትና ለኋላ ቀርነት የሚያጋልጠንን የጎሳ በሽታ ለመቀበል የምንሯሯጠው ለምን ይሆን?

ባጠቃላይ በድህነት አሮንቃ ውስጥ ገብቶ የሚማቅቀውን ወገን ወደ ተሻለ የዕድገት ደረጃ ለመምራት ሁሉም ዜጋ በቅንነትና በአንድነት በመሥራት ዛሬ በረሃብና በኋላ ቀርነት

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion

የምትጠራዋን ኢትዮጵያ ሳይሆን በአልደፈር ባይነቷና ባንድነቷ የምትታወቀዋን ያቺን ኢትዮጵያን ለልጆቻችን አቆያተን ለማስረከብ መሥራት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ አገራችን ናት።
ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ናቸው።
ኢትዮጵያዊነት ዜጋነታችንና ኩራታችን ነው።
ኢትዮጵያና አንድነቷ ለዘላለም ይኖራሉ።

**አሜን**

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!